# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር 219305

ጥቅምት 03 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ወ/ሮ በየነች ነጋሽ፡- ወኪል ብርሃን ገዙ ቀረቡ

ተጠሪ፡- መሰረተ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ምስራቅ ሆሳዕና አጥቢያ ፡-ጠበቃ አማኑኤል ዮሀንስ ቀረበ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በቀን 06/05/2014 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.17323 በቀን 12/02/2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት መሆኑን ገልፀው በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ መነሻ ያደረገ ሲሆን አመልካች በሀዲያ ዞን ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበሩ ሲሆን ተጠሪ ተከሳሽ ነበረች፡፡

የአሁን አመልካች በስር ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ ባቀረቡት የመፋለም ክስ አመልካች አዋሳኙ በክስ ዝርዝር ውስጥ የተጠቀሰውን በሆሳና ከተማ ሔጦ ቀበሌ መንደር 10 ሁለት ጥማድ ይዞታ ግብር በመገበር የምጠቀምበት ይዞታ ለአሁን ተጠሪ 1000 ካ.ሜ ላይ የተሰራ ሁለት ክፍል ቤት በሽያጭ አስተላልፌ ቀሪ 3000 ካ.ሜ ይዞታ እርሻ እያረስኩኝ በአንድ በኩል ሳር አሳድጌ በመሸጥ የምጠቀምበት

በዙሪያው ዕዶች ባህርዛፍ ተክዬ ያለውን ይዞታ የሆሳዕና ከተማ ማዘጋጃ ቤት ለልማት እፈልጋለሁ ብሎ ግምት ሳይሰጥ በመቅረቱ በእጇ ያለውን ይዞታ ተጠሪ ሐምሌ 19 ቀን 2012 ዓ.ም ወርረው በማጠር የያዙት በመሆኑ ይዞታውን ለቀው እንዲያስረክቡኝ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ በሰጠችው መልስም የክርክሩ ይዞታ በ2007 ዓም በተሰራው የአካባቢ ልማት ፕላን ለማህበራዊ አገልግሎት እንዲውል የተደረገ በመሆኑ በህጋዊ መንገድ ለተጠሪ የተሰጠ የተጠሪ ይዞታ ነው፤ይዞታው ከመነሻውም የአመልካች ሳይሆን የእህታቸው አዳነች ነጋሽ በመሆኑ ካሳ ብር 39,760.00 ስለተከፈላቸው፣አመልካች ያቀረቧቸው የግብር ደረሰኞች ለሌላ ቦታ የተገበረባቸው እንጂ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት የሌላቸው በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክራለች፡፡

የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ምስክሮች ሰምቶና ተገቢውን ማጣራት አድርጎ በሰጠው ውሳኔም አከራካሪው ይዞታ ከመነሻው የአመልካች መሆኑን በቀረቡት ማስረጃዎች የተረጋገጠ መሆኑን፤ማዘጋጃ ቤቱ አከራካሪውን ቦታ ተገቢውን ካሳ ለአመልካች በመክፈል ምትክ ቦታ በመስጠት 18 አመት ለሞላቸው ለአመልከች ሁለት ልጆች ምትክ ቦታ በመስጠት ቦታውን ሊያስተላልፍ ሲገባ ይህንን አለማድረጉ ስህተት መሆኑን፤ይዞታውን ማዘጋጃ ቤቱ የተጠሪን የማስፋፊያ ጥያቄ መሰረት በማድረግ ያስተላለፈላት መሆኑን ከምስክሮቹ ቃል ማረጋገጡን፤መሬቱ በተጠሪ የተያዘው በዚሁ አግባብ በመሆኑ ተጠሪ 3000 ካ.ሜ ቦታ አጥር በማጠር የያዘችውን አጥሩን አፍርሳ ልትለቅ አይገባም፤ የአሁን አመልካች ለተወሰዳባት ይዞታ መሬት የካሳ ግምት ብር 39,760.00 በስም አፃፃፍ ስሕተት በወ/ሮ አዳነች ነጋሽ ስም በዝግ አካውንት የተቀመጠውን ገንዘብ ወጪ ተደርጎ ለአመልካች እንዲሰጣት፤ የሆሳዕና ከተማ ማዘጋጃ ቤት ከሄጦ ቀበሌ ማዘጋጃ ቤት ጋር በመተባበር የአሁን አመልካች ልጆች ምትክ ይዞታ ያለማግኘታቸው በተደረገው የምትክ ዳኝነት ማጣራት ስራ የተረጋገጠ በመሆኑ ለሁለት ልጆቿ ለእየአንዳንዳቸው ሁለት መቶ ካ.ሜ በድምሩ 400 ካ.ሜ ይዞታ እንዲሰጥ በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በበኩሉ የስር ፍርድ ቤት ሰጠውን ውሳኔ በማፅናት የአሁን አመልካች የካሳ ገንዘብ መጠን ላይ ቅሬታ የማቅረብ መብቷን በመጠበቅ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ከዚህ ነጥብ አንፃር ብቻ በማሻሻል ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካች የባለይዞታነት መብት ሳትጠበቅ ከሕግ አግባብ ውጪ በኃይልና በጉልበት ይዞታውን ስለመያዛቸው የተረጋገጠ ጉዳይ ሲሆን የከተማ መሬት በሊዝ ስለመስጠት የወጣውን ደንብ ቁጥር 123/07 ለማስፈፀም ተሻሽሎ የወጣው መመሪያ ቁጥር 08/07 አንቀጽ 7(3)(ሀ) የገበሬ ልጆች የእርሻ ይዞታ ወደ ከተማ ሲጠቃለል ከባለይዞታው ጋር አብሮ በቋሚነት ለሚኖሩ ልጆች ለእያንዳንዳቸው 200 ካ.ሜ እንዲሰጥ ይደነግጋል፡፡ከቦታው ለሚነሳው ሰው ምትክ ቦታም ይሁን ካሳ የሚሰጠው በቅድሚያ እንጂ የያዘውን ይዞታ በሕገ ወጥ መንገድ እንዲለቅ ተደርጎ በኋላ የሚሰጥበት የሕግ አግባብ የለም፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመልካች የቤተሰብ ድርሻ አልተሰጠም በተሰጠው ውሳኔ መሰረት ለሁለቱ ልጆች ድርሻ ይሰጣቸው በሚል አፈፃፀም እንዳላቀርብ ማዘጋጃ ቤቱ የክርክሩ አካል አይደለም፤ በተጨማሪነትም አዲስ ክስ እንዳላቀርብ በእጄ ያለው ይዞታ መብቴ በፍርድ ቤት በጉልበት እንዲሄድ ተደርጎ የጠበቃ እንዲሁም የክርክር ወጪ ከፍዬ እንደገና ከማዘጋጃ ቤት ጋር መከራከር በራሱ በሕገ መንግስት አንቀጽ 40(8) ላይ የተመለከተውን መሰረት ያላደረገ ነው፤ ፍርድ ቤት ባለይዞታውን አፈናቅሎ መብት እንዲጣስ ውሳኔ መስጠቱ አላግባብ ነው፡፡

አመልካች የይዞታ ባለመብት ስለመሆኔ እስከ ቦታው ድረስ ሄዶ አረጋግጧል፡፡ከአመልካች የተወሰደው 3000 ካ.ሜ በላይ ሆኖ እያለ ብር 39,760.00 ይከፈል ማለት በራሱ ሕግን የሚቃረን ነው ይህ የተባለው ገንዘብ በአንድ አመት ምርት የሚሸፈን ገንዘብ ነው፡፡የካሳ ስሌትም በሕግ አግባብ ከአመልካች ጋር ድርድር ተደርጎ በመንግስት የካሳ ስሌት መሰረት የተሰላ መሆን አለመሆኑን ሳይረጋገጥ ገንዘብ ወጪ ተደርጎ ይሰጥ ማለት ሕግን የሚቃረን ነው፡፡የመሬት ይዞታ ለሕዝብ ጥቅም እንዲለቀቅ የሚደረገው በመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ወይም በከተሞች መዋቅራዊ ዕቅድ ወይም በመሰረተ ልማት መሪ ፕላን መሰረት መሆን አለበት ለህዝብ ጥቅም ወይም ለልማት እንጂ ለቤተክርስቲያን ለመስጠት ይዞታ ማስለቀቅ፣ ካሳ መክፈል አይቻልም፣ ከአመልካች ጋር የተደረገ ድርድርም ሆነ አንድም ማስጠንቀቂያ የለም፣ ቦታውን የያዙት በወረራ ነው በማለት ስከራከር ይህን ሁሉ አረጋግጦ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይዞታዬ እንዲወሰድ ከወሰነ በኋላ በድጋሚ የካሳ ክፍያ አንሷል የምትል ከሆነ በአስተዳደር አካል መጠየቅ ትችላለች በሚል መወሰን በቅድሚያ ካሳ መከፈል ይገባል የሚለውን የሕግ ጽንሰ ሀሳብ ጋር የሚጋጭና መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ነው፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍርድ ቤቶች ይዞታዬ በተጠሪ በኃይልና በጉልበት የተያዘው ይዞታ መሆኑን አስረድቼ ፍርድ ቤቱም አረጋግጦ እያለ፣ የቤተሰብ መብት ያልተከበረ ተገቢ ካሳ ተከፍሎ ከአመልካች እጅ ያልወጣ ለመሆኑ ተረጋግጦ እያለ ይዞታዬ እንዲወሰድ ከተወሰነ በኋላ የሚገመትበት ስርዓት ስለሌለ፤ንብረቱ ከእጄ ሳይወጣ የተነሺ መብት እንዲከበር እንጂ ለቀሺ ጠይቂ መባሉ በራሱ ህግን የሚቃረን በመሆኑ ተጠሪ ይዞታውን ልትለቅ አይገባም በማለት መወሰኑ የይዞታ መብቴን ያሳጣኝ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት መታረም የሚገባው ነው በማለት አመልክተዋል፡፡

በግራ ቀኙ መካካል ያለው ክርክር ከአመልካች ይዞታ ላይ ለተጠሪ የተሰጠው አዋጅን በተከተለ መንገድ ነው ወይስ አይደለም? ተጠሪ ቦታውን በሕጋዊ መንገድ ለባለይዞታው ካሳ ተከፍሎ ስልጣን ባለው አካል የተነሱ መሆን አለመሆኑን እና ፍርድ ቤቱ በሥነ ሥርዓት ሕጉ መሰረት ጭብጥ ለይቶ የወሰነ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ተጠሪ በሰጠችው መልስም ይዞታው ለተጠሪ የተሰጠው በሕግ አግባብ መሆኑን የሚያረጋግጠው ለአመልካች ቤተሰቦቿ መኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ 18 ዕጣ ወይም 4500 ካ.ሜ መሬት መስጠቱ ነው፡፡የስር ፍርድ ቤት ለአመልካችና

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ቤተሰቦቿ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ መሰጠት አለመሰጠቱን ከሆሳዕና ከተማ ማዘጋጃ ቤት ከተጠሩ ባለሙያዎችና በቦታ ምልከታ ወቅት የተረጋገጠ ሲሆን የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ላልተሰጣቸው የቤተሰብ 2 አባላትም ቢሆን አመልካች ያልጠየቀችው ዳኝነት ቢሆንም ማዘጋጃ ቤቱ ቦታ እንዲሰጣቸው ወስኗል፡፡የስር ፍ/ቤት በክርክሩ ሂደት ከግራ ቀኞችን ክርክርና ማስረጃ፣ ከማዘጋጃ ቤት እንዲቀርብ ካደረገው ማስረጃና በቦታ ምልከታ ከጣራቸው ፍሬ ነገሮች በመነሳት የክርክሩን ይዞታ ተጠሪ የያዘችው በሕጋዊ መንገድ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍበት አንድም ምክንያት የለም፡፡ስለሆነም አመልካች ይዞታዋ በተጠሪ በኃይል እንደተወሰደ በማድረግ የምታቀርበው ክርክር በስር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ የተጣሩ ፍሬ ነገሮችን መሰረት ያደረገ አይደለም፡፡

አመልካች ይዞታው ለተጠሪ የተሰጠው ስልጣን ባለው አካል አይደለም በማለት የሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት የሊዝ አፈፃፀም ደንብ ቁጥር 123/2007 እና የሊዝ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 08/2007 የምታቀርበውን ክርክር በተመለከተ የሀይማኖት ተቋማት የአምልኮ ቦታ የሚሰጠው በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት የከተማ ልማትና ቤቶች ቢሮ መመሪያ ቁጥር 17/2008 በተደነገገው መሰረት ነው፡፡በመመሪያው አንቀጽ 5(1) የአምልኮ ቦታ የሚዘጋጀው በከተማው ማዘጋጃ ቤት አማካኝነት ሲሆን ለአምልኮ አገልግሎት የሚውል ቦታ ነፃ ለማድረግና ተነሺዎችን መልሶ ለማስፈር የሚወጣውን ሙሉ ወጪ የሀይማኖት ተቋሙ እንደሚከፍል በአንቀጽ 5(6) እና በአንቀጽ 6(11) በግልጽ ተደንግጓል፡፡ተጠሪ የተጠቀሰውን የካሳ ገንዘብ የከፈለችው በዚሁ አግባብ ነው፡፡አመልካች ለአረንጓዴ ስፍራነትና ለመንገድ ብር 241,2409.93 ካሳ ተወስኖ የተወሰደባትን ይዞታ፣ ለተጠሪ የሸጠችውን ቤት ያረፈበትን 1000 ካ.ሜ እንዲሁም ለሌላ ባለይዞታ ካሳ ተከፍሎ ለተጠሪ የተሰጣትን 600 ካ.ሜ ይዞታ አንድ ላይ በመደመር ተጠሪ 3000 ካ.ሜ ይዛብኛለች በማለት የምታቀርበው ክርክር አግባብነት ያለው አይደለም፡፡

የክርክሩ ይዞታ ለተጠሪ በሕጋዊ መንገድ መሰጠቱ ተረጋግጦ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ከተሰጠና ዕገዳው ከተነሳ በኋላ 2,000,000 ብር በላይ የሚያወጣ ግንባታ ወይም ለቢሮ አገልግሎት የሚውሉ ቤቶችን ከሰራች በኋላ ይዞታውን በሕገ ወጥ መንገድ ይዛለች ትልቀቅ በማለት አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረበችው አቤቱታ አግባብነት የሌለው በመሆኑ አመልካች ያቀረበችው የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ የክርክሩ ይዞታ የተጠሪ ነው ተብሎ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲፀና እንዲወሰን በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

በአጠቃላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የሰበር ክርክሩን ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ፤ከተገቢው ሕግና ከስር ፍርድ ቤት ክርክር አንፃር እንደሚከተለው መርምረናል፡፡በመሰረቱ አንድ ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አወሳስን የጠራ ፍሬ ነገር የሌለ መሆኑን ከተገነዘበ ይኸው ፍሬ ነገር እንዲጣራ ተገቢ ነው ያለውን ማጣራት ሁሉ ማድረግ እንደሚችል ከፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.136፣137፣272 እና 345

ድንጋጌዎች ለመረዳት የሚቻል ሲሆን  ለጉዳዩ አወሳሰን መሰረት የሚሆንን ፍሬ ነገር በማስረጃ ሳያጣሩ መወሰን አግባብ ባለመሆኑ በክርክሩ የቀረቡት ማስረጃዎች በቂ ባልሆኑበት ጊዜ እና እነዚህን ማስረጃዎች ብቻ መሰረት አድርጎ መወሰን ፍትህን የሚያዛባ ከሆነ ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት ተጨማሪ ማስረጃ ወይም ምስክር እንዲቀርብ መታዘዝ ያለበት ስለመሆኑ በሰበር መዝገብ ቁጥሮች 72980፤22603 እና በሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች  አስገዳጅ የህግ ትርጉም ተሰጥቷል፡፡በዚህ አግባብ ፍርድ ቤቱ ተገቢውን ማጣራት አድርጎ የሚሰጠው ውሳኔ ተገቢውን የህግ ውጤት እንዲያገኝ በክርክሩ የግድ ተካፋይ መሆን ያለባቸውን 3ኛ ወገኖች በክርክሩ በማካተት ተገቢውን ውሳኔ ሊሰጥ የሚገባ ሲሆን በክርክሩ ውስጥ የግድ ተካፋይ መሆን የሚገባቸው ወገኖች ማለት ክስ በቀረረበት ጉዳይ ላይ በሚሰጠው ውሳኔ ጥቅማቸው፤መብታቸው ወይም ግዴታቸው የሚነካ ነገር ግን በክርክሩ ውስጥ ተካፋይ ያልሆኑ ሰዎችን የሚያመለክት ሲሆን በክርክሩ የግድ ተካፋይ መሆን ያለባቸው ተካፋይ ሳይሆኑ የሚሰጠው ውሳኔ ወይም ፍርድ ውጤት የማይኖረው በመሆኑ በክርክሩ የግድ ተካፋይ መሆን ያለባቸው ወገኖች በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.40(2) መሰረት የክርክሩ ተከፋይ መደረጋቸውን ፍርድ ቤቱ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

አሁን በያዝነው ክርክር አከራካሪው ይዞታ ከመነሻው የአመልካች መሆኑ ማስረጃን የመስማት፤የመመርመርና የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ በመሆኑ እና ተጠሪ አከራካሪው ይዞታ በ2007 ዓም በተሰራው የአካባቢ ልማት ፕላን ለማህበራዊ አገልግሎት እንዲውል የተደረገ በመሆኑ በህጋዊ መንገድ የተሰጠኝ ይዞታዬ ነው በማለት እየተከራከረች በመሆኑ ፤ይህ ይዞታ ተሰጠኝ የምትለው በከተማው ማዘጋጃ ቤት መሆኑን ጠቅሳ እየተከራከረች በመሆኑ ማዘጋጃ ቤቱ ወደ ክርክሩ ገብቶ አከራካሪው ይዞታ በአካባቢ ልማት ፕላን መሰረት ለማህበራዊ አገልግሎት እንዲውል በተገቢው አካል ተወስኖ ለተጠሪ የተሰጠ ነው? ወይስ አይደለም? በዚህ አግባብ የተሰጠ ውሳኔ ካለም በዚህ አግባብ ከመወሰኑ በፊት አመልካች ስለልማቱ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ እንዲሁም ስለ አጠቃላይ ሂደቱ እንዲያውቁና እንዲወያዩ ተደርጓልን?ስለሚነሳው ንብረት የባለቤትነት ማስረጃ ከመሰብሰብ ባለፈ የልኬትና መጠን መረጃ በመሰብሰብ፤በተሰበሰበው ማስረጃ መሰረት የካሳ መጠን እና/ወይም ምትክ ቦታ ስፋትና አካባቢን ወይም ቤት በመግለፅ በፅሁፍ የማስለቀቂያ ትዕዛዝ ለአመልካች ተሰጥቷልን? በማስጠንቀቂያው አግባብስ ተገቢው ካሳ እና/ወይም ምትክ ቦታ ተሰጥቷቸዋልን? በአጠቃላይ አመልካች አከራካሪውን ይዞታ እንዲለቁ የተደረጉት በህጉ አግባብ ተገቢውን ቅድመ ሁኔታ በማሟላት ነው ወይስ እነዚህ ሳይሟሉ በአመልካች ክስ እንደተገለፀው በሀይል ተግባር? የሚሉትን ነጥቦች በአግባቡ በማጣራት የስር ፍርድ ቤት ለግራ ቀኙ ክርክር እልባት መሰጠቱን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ አያሳይም፡፡

የስር ፍርድ ቤቶች ከላይ በተመለከተው አግባብ ተገቢውን ማጣራት ሳያደርጉ ማዘጋጃ ቤቱ የክርክሩ ተካፋይ ባልሆነበት የአመልካችን ይዞታ ይለቀቅልኝ ክስ ውድቅ በማድረግ ለቤተሰብ አባላቱ ምትክ ቦታ እንዲሰጥና ለአመልካች ካሳ እንዲከፈል መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘው ተከታዩን ወስነናል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

# ውሳኔ

1. የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.22240 በቀን 13/04/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እና ይህንን ፍርድ በማሻሻል የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.17323 በቀን 12/02/2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጉዳዩን መዝገብ በማንቀሳቀስ ማዘጋጃ ቤቱን ወደ ክርክሩ በማስገባት የግራ ቀኙን ክርክር ከላይ በፍርዱ ዝርዝር በተመለከተው አግባብ በመምራትና ተገቢውን ማጣራት በማድረግ በህጉ አግባብ የመሰለውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.343(1) አግባብ መልሰንለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

<u>ጉዳዩ ውሳኔ ስለገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡</u>

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም